# አብዮታዊት ኢትዮጵያ 18




ጥር ፲፰—፲፱፻፸፱ ዓ·ም·

**ለውይይት መነሻ**

አብዮታዊት ኢትዮጵያ ከቊጥር ፩ ጀምራ «ለነማርክስ ፍልስፍና አጭር መግቢያ» በሚል ርእስ ሥር በተከታታይ ትምህርታዊ የሆኑ የፍልስፍና ጽሑፎች ታቀርባለች ። እነዚህ ጽሑፎች የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ገና ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚተዋወቁ የውይይት ክበቦች መነሻ ሃሳቦች እንደሚሰጡ ሆነው የቀረቡ ናቸው።

# መንግሥትና ሕግ

## ፲፫ኛ ትምህርት ከን.ዓ.

ቀደም ሲል መንግሥት የሚባለው ድርጅት አንዱ መደብ ሌላውን መደብ ጨቁኖ የሚገዛበትና ጥቅሙን የሚያስከብርበት የማስገደጃ ድርጅት መሆኑን ገልጸናል ። መንግሥት ሕግ ለማስከበር የቆመ ድርጅት ነው ። የሚያሠልፈው ሠራዊት ፖሊስ ፤ ዳኛ ፤ ፍርድ ቤት . . . . ሁሉ የሚቆመው አንድ የተወሰነ ሕግ ከሥራ ላይ ለማዋል ፤ ያንን ሕግ የሚጥሱትን ግለሰቦች ለመቅጣትና ያንን ሕግ ለማስከበር ነው ። ስለሆነም መንግሥት የተባለው ነገር የቆመው ለዚህ ዓላማ ከሆነና ሕግ የሚባለው ደግሞ እገሌ ከእገሌ ሳይል ለሁሉም እኩልና የማያደላ ከሆነ መንግሥት ያደላል ፤ የመደብ መሣሪያ ነው የሚባለው የት ላይ ነው ይባል ይሆናል። ነገር ግን ነገሩን ጠለቅ ብሎ ላየ ሰው ሕግ የሚባለው ነገር ራሱ የመደብ ይዘት አለው ። ለሁሉም እኩል የሚጠቅም ፤ ለጠቅላላው ኅብረተሰብ የጋራ ጥቅም ያገለግላል ተብሎ የሚቆም ሕግ የለም ። ሕግ ያደላል ። እንዲያውም ሕግ ባያዳላ ኖሮ እሱን ለማስከበር የቆመው መንግሥት የሚባለው ማስገደጃ ድርጅት የመደቦች ጥቅም ማስጠበቂያ ድርጅት ባልሆነ ነበር ።

እንግዲህ ማርክሲስቶች ሕግ የመደብ ይዘት እንዳለው ያምናሉ ። አጼ ኃይለ ሥላሴ በዘመናቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰጠሁ ይሉት ስለነበረው « ሕገ መንግሥት » ባወሱ ቁጥር « ማንም ሳይጠይቀን በገዛ መልካም ፈቃዳችን ለምንወደው ሕዝባችን የሰጠነው » እያሉ ይወተውቱ እንደነበረ ግልጽ ነው ። ማርክሲዝምም ስለሕግ ጉዳይ ሌላ ብዙም የሚለው ነገር የለም ። የበላይነት ያለው መደብ መልካም ፈቃድ ነው ። « ሕግ ማለት » ይላል «ሌኒን ሕግ ማለት የተደነገገ የገዥው መደብ መልካም ፈቃድ ማለት ነው ። » ጠቅላላውን የመንግሥቱንና የሕግን ታሪክ ስንመለከት የምናየው ይህንኑ ሳይንሳዊ ሐቅ ነው ።

በባርያ ገዥዎች ሥርዓት እንጀምር ። ለምሳሌ በጥንት ጊዜ የነበረውን የሀሙራቢን መንግሥት ሕግጋት እንመልከት ። የሀሙራቢ ኮድ ወይም ሕግ እየተባለ ሲወርድ ሲዋረድ እስከዛሬ የመጣልን የሕግ መጽሐፍ አለ ። ይህ የሀሙራቢ ሕግ በዓለም እጅግ ከታወቁና ከተደነቁ ታላቅ ከሚባሉት የሕግ መጻሕፍት አንዱ ነው። ነገርግን ይህ የሐሙራቢ ኮድ ሀሙራቢ ይገዛው የነበረበት ሥርዓት የባርያ ገዥ ሥርዓት እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ የከበርቴ አፈቀላጤዎች ሊሉ እንደሚሞክሩት ለጠቅላላ ኅብረተሰቡ ጥቅም የቆመ ሕግ አልነበረም ። ይህንን ለመረዳት ገለጥ አድርጎ የሕጉን ይዘት መመልከት ይበቃል ። ሕጎቹ የሚጠብቁት የባርያ ገዥዎችን መደብ ጥቅም ነበር። ስለሆነም ከአንቀጾቹ አብዛኛዎቹ ባርያ እንዴት እንደሚሸጥ ፤ እንዴት እንደሚለወጥ ፤ ባርያው « የተደበደበበት » ባርያ ገዥ ስንት ካሣ እንደሚገባው ፤ « የሰው » ባርያ የገደለ ለባለቤቱ ምን እንደሚከፍል ፤ መልሶ « ከራሱ » ባርያዎች አንዱን እንዴት መተካት እንዳለበት ባርያ በውርስ ወይም በስጦታ ስለሚተላለፍበት ሁኔታ አንዳችም ዓይነት አለመግባባት በማይኖርበት ሁኔታ እየዘረዘረ ያስቀመጠው መጽሐፍ ነበር ። ኅብረተሰቡ የተመሠረተው በዚሁ በባርያ ጉልበት ላይ ስለነበረ በዚህ በኩል አንድ ዜጋ ያለውን « የግል ሀብት » መብት መተናኮል በምንም ዓይነት ይቅርታ የማይደረግለት ጉዳይ ነበር ። እንኳን «ጠቅላላውን ባርያ ሁሉ ነፃ ይውጣ » ብሎ ሥርዓቱን የሚያናጋ ይቅርና አንድ ባርያ ሰርቆ የተገኘ እንደሆነ እንኳን « በሕጉ መሠረት » እስከሞት የሚቀጣበት ሁኔታ ነበር።በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉት ብዙኃኑ ባርያዎች ነበሩ ። ይኸ ሕግ እንኳን የነዚህን ብዙኃኑን ጥቅም ሊያስከብር ይቅርና « ከሚናገሩ መሣሪያዎች » አስበልጦ አይመለከታቸውም ነበር ።

ወደዚህ ወደኛ ቀረብ ብለን በፊውዳል ኢትዮጵያ የነበረውን ሕግ እንመልከት ። ከፍ ብለን ያወሳነውን ሕገ መንግሥት ልብ ብለን ብንመለከተው የማንን ክብርና ሥልጣን የሚያስከብር ሕግ ሆኖ እናገኘዋለን ? ይህ ሕገ መንግሥት ይዘቱ ሲታይ አብዛኛው ክፍል ስለአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ ዘለዓለማዊነት ፤ ስለንጉሠ ነገሥቱ የማይገሠሥ ክብር ፤ ስለማይደፈረው ሥልጣኑ ፤ አንድ ንጉሥ ሲሞት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለስንት ወር ሙሉ ኀዘን እንደሚያዝን ፤ በግማሽ ኀዘን ተቆጥቦ ስንት ወር መቆየት እንደሚኖርበት ፤ የንጉሥ ሚስት ከሆነች የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ምን ያህል ሙሉ ኀዘን እንደሚወድቅበት ፤ የግማሽ ኀዘኑ ጊዜ ስንት እንደሆነ ፤ የቤተ መንግሥት ዘር ከሆነ አንድ ዜጋ ገና በእናቱ ማኅፀን እንዳለ ስለሚሰጠው ክብርና የውርስ መብት . . . . ይህን ይህን ሁሉ እየዘረዘረ የሚያስረዳ ሕግ ነበር ። እርግጥ በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ ለላንቲካ ያህል ስለኢትዮጵያ ሕዝብ መብቶች ተወስተዋል ። ግን በዚያ ሕገ መንግሥት ውስጥ የተጠቀሱት መብቶች በፍጹም ከሥራ ላይ ውለው እንደማያውቁ ግልጽ ነው ።

ከዚያም ወዲህ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የወጣውን የፍትሐ ብሔር ሕግ እንመልከተው ። እርግጥ አጼ ኃይለ ሥላሴ ይህንን ሕግ በደነገጉበት ወቅት « ለሚወዱት ሕዝባቸው » ጥቅምና ብልጽግና የሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት ለማስጠበቅ የተደነገገ አድርገው አቅርበውታል። ግን ይህ ሕግ በርግጥ ለጠቅላላው ለኢትዮጵያ ኅብረተሰብ የቆመ ሕግ ነበር ወይ ? አልነበረም ። የአብዛኛውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም በሚመለከተው በኩል ብናየው አንዱ አንቀጽ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ለጥቂት ባለርስቶች የሥራ ፍሬያቸውን ማስረከብ ስላለባቸው ግዴታ ሲያወራ ከምርታቸው እስከ ፸፭ በ፻ ድረስ ለባለርስት መስጠት እንዳለባቸው ይናገራሉ ።

እንግዲህ ይህንን ሕግ « ጥቅሜን ይጐዳኛል» ትክክል አይደለም » ብሎ የሚቃወምስ ? የለም አልገብርም አሻፈረኝ የሚልስ ? እንዲህ ዓይነቱ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ላይ ያመጸ ሕገወጥሽፍታ ተብሎ በሕጉ መሠረት እንዲቀጣ « ከፍርድ ፊት» በጸጥታ አስከባሪዎች « ተይዞ ይቀርባል » « በሕጉ መሠረት » አንቀጽ በአንቀጽ እየተጠቀሰ ይፈረድበታል ። ይቀጣል ።

ዛሬስ ? ዛሬ ደግሞ ይኸ ሁሉ ተለውጦ በኢትዮጵያ የፊውዳሉ ሥርዓት እየፈራረሰ አዲስና ሕዝባዊ ሥርዓት በመገንባት ላይ ነው ። ያለፈውን መንግሥትና ሕግ በመሻር አዲስ የሕዝቡን ጥቅም ሊያረጋግጥ የሚችል ፀረ ፊውዳል የሆነ የመሬት ዓዋጅ ወጥቷል ። በዚህ ዓዋጅ መሠረት የኢትዮጵያ ድሀ ገበሬዎች ለባለርስት ከመገበር ነፃ ሆነዋል ። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው« በባለርስትና በጢሰኛነት መሐከል የነበረው ግንኙነት ኤርቧል» ሙቴስ ሕግ ሲባል « የጠቅላላውን ኅብረተሰብ ጥቅም » የሚጠብቅ ነገር ሳይሆን የአንዱን መደብ ጥቅም የሚጠብቅ በመሆኑ ሕጉን አንቀበልም በማለት ቀደም« ሕግ አስከባሪ » « ትልቅ ሰው » እየተባሉ ይገሙቱ የነበሩ ፊውዳሊስቶች ዛሬ ሕገ ወጥ ሽፍታ ሆነው በሠፈሩት ቁና በመሠፈር ላይናቸው። ዱሮ አልገብርም የሚል በሕጉ መሠረት ይቀጣ ነበር ። ዛሬ ደግሞ ሳይሠራ አስገብሬ እኖራለሁ የሚል በሕጉ መሠረት አንቀጽ እየተጠበቀ የሚቀጡበት ጊዜ ነው ።

እንዲህ ዓይነቱ የኅብረተሰብ ሽርሽር ደግሞ የማይቀር ነገር ነበር ። መንግሥትና ሕግ የመደቦች መሣሪያ እንደሆኑ ፤ እንደሚያዳሉና« በሕጉ መሠረት » ስለተሠራ ብቻ አንድ ድርጊት ከመደቦች ትግል ውጭ ሊታይ እንደማይችል ከስምንት ዓመታት በፊት« ትግላችን » በአውሮጳ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ወርኃዊ መጽሔት የሚከተለውን ጽፎ እናገኛለን ። « የትግላችን » ጽሑፍ የተነሣው ሚቸልኮትስ ከሚባለው መሥሪያ ቤት ፲፱ ሠራተኞች እንዲባረሩ ተወስኖባቸው ይህ ድርጊት ባስከተለው ክርክር የጊዜው የኢ.ሠ.አ.ማ.«የሕግ አማካሪ » የሠራተኞቹ መወገድ በሕጉ መሠረት ትክክል ነው ብለው በወሰዱት አቋም ላይ ለመተቸት ነበር ። ጽሑፉ እንዲህ ይላል ። በረዥሙ እንጥቀሰው ።

« የሕጉ አማካሪ ግን በጉዳዩ አስተያየታቸውን ሲሰጡ የሠራተኞቹ ከሥራ መወገድ ትክክል ነው ካሉ በኋላ ኩባንያው የወሰደው ርምጃ በኢትዮጵያ ተግባረ ሥራ ሕግ መሠረት በፍጹም ትክክለኛ ነው ይሉናል ። አለመግባባት ሆኖ ነው እንጂ እኛስ ሌላ ምን አልን ?

በሕጉ መሠረት የኢትዮጵያ ሠራተኞች ደማቸው እየተመጠጠ ሲያልቁ እንደደረቀ ሎሚ ይወረወራሉ ። « በሕጉ መሠረት » የኢትዮጵያ ገበሬዎች ካለባቸው ፍሬ ፸፭በ፻ እንዲሰጡ ይገደዳሉ። « በሕጉ መሠረት » አንድ ሕዝብ በሙሉ ተሠልፎ ለጥቂቶች ምቾት ይባክናል ! ይህ ታዲያ ምን ያሳየናል ? ግልጽ ነው ፤ ዛሬ በሀገራችን አለን የም

ንለው ሕግ » በጥቂቶች ተሰናድቶ ለጥቂቶች ጥቅም የቆመ ሕግ ነው ። ታዲያስ ? ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ ነውና ሀብታሞቹ ባወጧቸው ሕጋቸው እነሱው ቢጠቀሙበት ምን ያስደንቃል ?

« የሕጉ አማካሪ አልፈው ተርፈው » የኩባንያው ባለሥልጣኖች በዚህ ጉዳይ በተነሣው ክርክር« ከመጠን በላይ የሆነ የመተባበር መንፈስ አሳይተዋል » ይሉናል ። ይገርማል ! ይኸም ታዲያ ይብዛባቸው እንዴ ? የሠራተኛው አልሞት ባይ ተጋዳይነትና « አለመተባበር » በደንብ አድርጎ ይገባናል ። አይደነቁ ! የኢትዮጵያ ሕዝብ ካለመተባበርም አልፎ ጨቋኞቿን ጠራርጐ የሚጥልበትና ለእርሱ ታዛዥ የሆነ መንግሥት የሚያቆምበት ጊዜ ይመጣል ። ያኔ ታዲያ ሕጉ ለወዝ አደሩ እንደሚያመች ሆኖ ይወጣና « እንዝረፍ ፤ እናስገብር ፤ ተቀምጠን እንግፈፍ» እያሉ ሲያወናብዱ የሚገኙ ሁሉ ወዮላቸው ! « በሕጉ መሠረት » እየታፈሱ ውንብድናቸውን እንዲያቆሙ ይገደዳሉ ።

እስከዚያው ግን ሠራተኞቹ በገዛ ሀገራቸው ለመሥራትና ለመኖር ያላቸውን መሠረታዊ መብት የተነፈጉት« በሕጉ መሠረት » ነው የሚሉት ማስረጃም ያስገኘው ውጤት ቢኖር ሕዝቡ የመንግሥቱ ሕግ በየት በኩል እንደሚያዘነብል እንዲያይ ማስቻሉ መሆኑን እናስታውሳት ። ሕጉ በሀብታሞች ስለታወጀ ለሀብታሞች ያደላል ። የመላው የኢትዮጵያን ሕዝብ መብትና ጥቅም የሚጠብቅ ሕግ ሊኖር የሚችለው የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አለኝታ የሚሆን ሕዝባዊ መንግሥት ሲኖር ብቻ ነው »

ታዲያ የማያዳላ ሕግ የለም ። የማይጨቁን መንግሥት የለም። ታዲያ በጠቅላላው መንግሥት የሚሉ ነገር ዛሬውኑ ጨርሶ ይውደም ። በጠቅላላው መንግሥትን ሁሉ እንቃወም ? ከዚህ ሐቅ ተነሥተው አንዲህ ዓይነቷ መደምደሚያ ላይ የሚደርሱ« አናርኪስት » የሚባሉት የከበርቴና ንዑስ ከበርቴ ደንፊ ተራማጆች ናቸው ። ከነሌኒን ጋር የሚያጋጯቸው ጉዳይ አናርኪስቶች የካፒታሊስት ሥርዓት ከመንግሥት ሥልጣን በተወገደ ማግሥት መንግሥት የሚሉ ነገር አብሮ መጥፋት አለበት ሲሉ እነሌኒን ደግሞ « የለም የካፒታሊዝም በዝባዥ ሥርዓት ጨርሶ እንዲወድምና የወደቁት አድኃሪዎች ሙልሰው እንዲያንሠራሩ ወዝአደሩ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ የሚገዛበት መንግሥት ያስፈልገዋል ። መንግሥት የሚባለው ነገር እየመነመነ የሚጠፋው መደቦችም እየጠፉ ሲሄዱ ብቻ ነው ። » የሚል አቋም ስለሚወስዱ ነው ።

ይህ ማለት እንግዲህ ተራማጆች የሚቃወሙት ዓይነት መንግሥት ፤ የሚደግፉትና የሚታገሉለት ዓይነት መንግሥት አለ ማለት ነው ። ይህንን የሚያደርጉት በምን መለኪያ ነው ? የመንግሥቱ የመደብ ይዘት በስተቀር ሌላ ምንም መለኪያ የላቸውም ።

ከላይ እንዳልነው እስካሁን በታሪክ የታወቁት የበዝባዥ መንግሥታት ሦስት ዓይነት የመደብ ይዘት ያላቸው ናቸው ። የባርያ ገዥዎች መንግሥት ፤ የፊውዳሊስቶች መንግሥት ፤ የከበርቴዎች መንግሥት ፤ ብዙውን ጊዜ የባርያ ገዥዎች መንግሥት የሚወስደው ቅርፅ የአንድ አምባገነን ወይም የጥቂት አሪስቶክራቶች ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ነው። የፊውዳል መንግሥት ቅርፅ ከዘውድ አገዛዝ ጋር የተያያዘ ነው ። የከበርቴዎች መንግሥት ደግሞ ከሪፐብሊክ ጋር የተያያዘ ነው ። ግን በመደብ ይዘቱ እንጂ አንድን መንግሥት በቅርጹ ወይም በስሙ ብቻ መለካት አይቻልም ። በባርያ አገዛዝ ላይ የተመሠረቱ « ዲሞክራሲያዊ » ሕዝባዊ መንግሥታት ነበሩ ። ለምሳሌ በአቴንስ የባርያ መንግሥት ግን « ሕዝብ » ተብለው መንግሥት የመምረጥ መብት የተሰጣቸው በኅብረተሰቡ ውስጥ እፍኝ የማይሞሉት ባርያ ገዥዎችና የነሱ ወገኖች ብቻ ነበሩ ። በፊውዳሉም ሥርዓት እንደዚሁ በሕዝብ ምርጫ የሚቆሙ መንግሥታት ነበሩ ። ለምሳሌ እንደነቬነስ ዓይነቶቹ የጣሊያን የቀድሞ ሪፑብሊኮች እዚህ ላይ ግን « ሕዝብ » ሲባል የፊውዳሉ መደብ እንደሆነ ግልጽ ነው ። በከበርቴም መደብ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት ሲባል እርግጥ ሰው ሁሉ የመምረጥ መብት ቢኖረውም የምርጫው ስልት የሚዘጋጀው ፤ ከዚያም የሕዝቡን አስተሳሰብ ለመማረክ ጋዜጣው ፤ ሬዲዮው ፤ ቴሌቪዥኑ የሚጠይቀውን ሀብት ያለው ያው የኢኮኖሚ ኃይል ያለው ከበርቴው መደብ ነው ። ስለዚህም በካፒታሊስት ሥርዓት የሕዝብ መንግሥት የሚባለው የከበርቴ ጥቅም ጠባቂ መንግሥት ነው ። በዚህ ላይ የከበርቴዎች መንግሥት እንደ እንግሊዝ ፤ ጃፓን የተወሰነ የዘውድ አገዛዝ መልክም ሊወስድ ይችላል ። ስለዚህ የአንድን መንግሥት እውነተኛ ጠባይ ለማወቅ የመደብ ይዘቱን እንጂ ቅርጹን ብቻ መመልከት አይበቃም ። ማርክሲስቶች ለወዝደሩ አምባገነንነት መንግሥት የሚታገሉት ከዚህ ሐቅ ተነሥተው ነው ።